# የሄዋን ዕንባ

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*




«ወልዶ መሳም
ዘርቶ መቃም » እያማረኝ፤
ዕድሜዬ እየሸሸ ጥሎኝ፤
ጉልበቴ በሥራ ብዛት ደቆ፤
ማሕጸኔ በብስጭት ደርቆ፤
ሰብሳቢ አለሁ ባይ አገር አጥቼ፤
አነባለሁ በሰው አገር ወገኖቼ፤
ድረሱልኝ የወገን ያለህ እላለሁ፤
አገር ሞቶብኝ አለቅሳለሁ ፡፡

ጥርሶቼ መሳቅ ተነፍገው፤
በሃዘን ጥላ ተጋርደው፤
ዐይኖቼ ተርበው፤
የሚወዱትን ማየት ተነፍው፤
ከንፈሮቼ ርቋቸው ፈገግታ፤
ተሸብበው በዝምታ፤
ያፈቀሩትን ደረት ሳይንተራሱ፤
ጡቶቼ በደረቴ ላይ አነቡ አለቀሱ ፡፡

ሽንጤ በማፈቅረው ሳይታቀፍ፤
ዳሌዬ በወንድ ላይ ሳያሾፍ፤
ልቤ ጨቤ ሳይረግጥ ሳይጨፍር፤
ፍቅር ሰጥቼ ሳልቀበል ፍቅር፤

*ማሕጸኔ ረጥቦ ዘር ተክቼ፤
ዐይኔን በዐይኔ አይቼ፤
የናትነት ወጉ ሳይደርሰኝ፤
ወልዶ መሳም እያማረኝ፤
እኖራለሁ በበደል እየከፋኝ ፡፡*

*በቢላዎ ፋጩት በድስት ኳኳታ፤
በሹካና በማንኪያ ጬጬታ፤
ታጅቤ ከጠዋት እስከማታ፤
ተዘግቶብኝ ከቤት ሳልወጣ፤
ባርነት ሆኗል የኔ ዕጣ ፡፡*

*በንባዬ እየከለሰኩ የውስጤን ትኩሳት፤
ያልፍልኛል ብዬ ሌት ተቀን ሰዋትት፡፡
ጉልበቴን ጨርሼ ዕድሜዬን በላሁት፤
ሥጋዬን ዘልዝዬ በደሜ አጠቀሰኩት ፡፡*

*በሞት አጥር ታጥሬ ዕጮሃለሁ ፤
ያገር የወገን ያለህ እላለሁ ፤
አገር ሞቶብኝ አለቅሳለሁ ፤
ድረሱልኝ እላለሁ ፡፡*

*ኅዳር 1 ቀን 2002 ዓ.ም. (November 10 2009)
መብታቸውን የሚያስከብርላቸው አገር አተው በየአረብ አገሩ ለሚሰቃዩ እህቶቼ ማስታወሻ ትሁንልኝ፡፡*